የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፶፭
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No. 55
ADDIS ABABA,31st July, 2015


<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፩/፪ሺ፯ ዓ.ም


ለሁለተኛው ምዕራፍ የግብርና ዕድገት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ……………………………..ገጽ ፰ሺ፪፻፸፬


**<u>CONTENTS</u>**

Proclamation No. 911/2015


International Development Association Financing Agreement for the Second Agricultural Growth Project Ratification Proclamation …………….....……..Page 8274


## አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፩/፪ሺ፯

**<u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

ለሁለተኛው ምዕራፍ የግብርና ዕድገት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፪፻፵፰ ሚሊዮን ፫፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሁለት መቶ አርባ ስምንት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘውን የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ ሜይ ፯ ቀን ፪ሺ፲፭ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No 911/2015

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION</u>**

WHEREAS, a Financing Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association Provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit in an amount not exceeding SDR 248,300,000 (Two hundred forty eight million three hundred thousand Special Drawing Rights) for Financing the Second Agricultural Growth Project, was signed In Addis Ababa on the 7th day of May 2015;

WHEREAS, the House of people's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Financing Agreement at its session held on the 7th day of July 2015.

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለሁለተኛው ምዕራፍ የግብርና ዕድገት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፩/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>ስምምነቱ ስለመጽደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ ሜይ ፯ ቀን ፪ሺ፲፭ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 5605-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

**፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፪፻፵፰ ሚሊዮን ፫፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሁለት መቶ አርባ ስምንት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

**፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for the Second Agricultural Growth Project, Ratification Proclamation No 911/2015''.

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The financing Agreement Credit Number 5605-ET signed in Addis Ababa on the 7th day of May,2015, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of SDR 248,300,000 (Two hundred forty eight million three hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 31st day of July, 2015.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**